# አባላትና ሕዝብ እንዲያዉቁት!!!

የቅንጅት ድጋፍ አስተባባሪ ድርጅት በዩናይትድ ኪንግደም ከምርጫ 97 ማግስት ጀምሮ በሀገራችን መልካም አስተዳደርና የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን፣ የዜጎች ነጻነት፣ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ ሕዝብ የደምና የሕይወት መስዋዕትነት የከፈለበት ሰላማዊና ሕጋዊ የዴሞክራሲያ ሂደት እንዳይዳፈን የበኩሉን ድርሻ ለማበርከት የተቻለዉን ያህል ጥረት አድርጓል። አገዛዙ በሕዝብ ላይ የሚፈጸመዉን የሰብአዊ መብት ረገጣ እንዲያቆም፣ የሕዝብ ድምጽ እንዲከበር፣ የፓለቲካና የህሊና እስረኞች ከእስር እንዲለቀቁ በታላቋ ብሪታንያ የሚኖረዉ ኢትዮጵያዊ ድምጹን እንዲያሰማ የማስተባበር ሥራ ሠርቷል። ከለንደን እስከ ኤደምብራ፣ ብራስልስና ፍራንክፈርት ድረስ የተደረጉ የተቃዉሞ ሰልፎችን በግልና ከእህት ድርጅቶች ጋራ በቅንጅት አስተባብሯል። ከእንግሊዝ መንግስትና ከአዉሮፓ ፓርላማ፣ ከሌሎችም መንግስታዊ አካላትና የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅቶች ጋር ግንኙት በመፍጠር የምልጃና የዲፐሎማሲ ሥራዎችን ለማከናወን የአቅሙን ያህል ጥረት አድርጓል።

ከዚህም በተጨማሪም ከቅንጅት እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ ገዢዉ ሃይል በወሰደዉ አረመኔያዊ ጭፍጨፋ ሰለባ ለሆኑ ወገኖች ገንዘብ ለማሰባሰብና መጠነኛ ድጎማ ለማድረግ ከመቻሉም በላይ በእንግሊዝ አገር የሚኖረዉ ኢትዮጵያዊ በተለይም የድጋፍ ድርጅቱ አባላትና ደጋፊዎች በሀገራችን ወቅታዊ አንገብጋቢ ኩነቶች ላይ የበለጠ ግንዛቤ እንዲራቸዉ ሕዝባዊ የዉይይት መድረኮችን አዘጋጅቷል። ፓለቲካዊና ድርጅታዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ወቅታዊ መግለጫዎችን በማዘጋጀትና በመገናኛ ብዙሃን በማዉጣት ሕዝብ ስለ ጉዳዮቹ ግንዛቤ ለማስጨበጥ አቅም የፈቀደዉን ያህል ጥረት አድርጓል። በሀገራችን የተንሰራፋዉ ግፈኛ አገዛዝ በሕይወታቸዉ ላይ አደጋ እንዳያደርሰባቸዉ በመፍራት ወደ እንግሊዝ አገር ለተሰደዱ የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎች የተለያዩ የድጋፍ አገልግሎቶች ሰጥቶቷል። በሰፊ ሕዝባዊ መሠረትና በጠንካራ ድርጅታዊ አቋም ላይ ተመርኩዞ የተቀነባበረና የተቀናጀ ትግል ማካሄድ የሚኖረዉን ጠቀሜታ በማሰብ የተቋቋመዉ የአዉሮፓና የአፍሪካ የቅንጅት ድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች ምክር ቤት ተልዕኮ ይሳካ ዘንድ ድርሻዉን ለማበርከት በቀና መንፈስ ተንቀሳቅሷል። በአጠቃላይ ቅንጅት ዩኬ በሀገራችን የሚታየዉን ግፈኛ አገዛዝ ተወግዶ የዜጎች ሁሉ ነጻነትና ሰብአዊ መብቶች የተከበሩባት፣ መልካም አስተዳደር የሰፈነባት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ እንድትገባ ለሚደረገዉ ትግል ቅንጅት ያነሳዉን አርማ በማንገብ የተቻለዉን አድርጓል። በዚህም በአንድ ወቅት በሌሎች በተመሳሳይ መስመር ለሚንቀሳቀሱ ድጋፍ ድርጅቶች እንደ ሞዴል ይታይ የነበረ መሆኑን ብዙ ተመልካቾች ይመስክራሉ።

ይህ መልካም እንቅሰቃሴና ዉጤት የተገኘዉ ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ ስለነበረ ወይም አባጣ ጎርባጣ ዉጣ ዉረዶች ሳያጋጥሙ ቀርሪዉ ሳይሆን በሥራ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ከቅንጅት መሠረታዊ ዓላማዎችና መስመር አኳያ በማየት በወቅቱ የመቻቻል መንፈስ ስለነበረ፣ ሥራዎችን በመረዳዳትና በመግባባት በአንድነት ለመከወን በመቻሉ፣ እንደዚሁም ከተለያዩ አቅጣጫዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ይሰነዘሩ የነበሩ አፍራሽ ጣልቃገብነቶችን በአግባቡ በዘዴ ለመቋቋም በመቻሉ ነበር። ከምንም በላይ ግን አብዛኛዎቹ የአመራር አባላትና የድርጅቱ ደጋፊዎች ለቅንጅት በነበራቸዉ ጽኑ ድጋፍና ፍቅር ከዉስጥም ሆነ ከዉጭ የሚፈጠሩ መሰናክሎችን በጽናት መቋቋም በመቻላቸዉና ቅንጅት ይዞት የተነሳዉ የመቻቻልና የአንድነት መንፈስ የበላይነቱን ይዞ አንዲዘልቅ ለማድረግ በመቻላቸዉ ነበር። ድርጅቱ በራሱ ከነበረበት የአቅም አለመጎልበት ባሻገር በአንዳንድ የኮሚቴ አባላት ዘንድ የግል ዝናና ቡድናዊ ስሜት የመሳሰሉት ችግሮች ይንጸባረቁ የነበረ ቢሆንም የድርጅቱ ህልዉናና አንድነት ተጠበቆ ቆይቷል።



1Crowndale Road London NW1 1TU Tel/Fax: 020 7168 9893 E-mail: kinijit97@yahoo.co.uk

ይህ የአንድነት የመቻቻል መንፈስ የቅንጅት መሪዎች ከእስር ቤት እስከሚፈቱ ድረስ የዘለቀ ቢሆንም፣ የቅንጅት መሪዎች ከወህኒ ከወጡ በኋላ ግን በመካከላቸዉ የተከሰተዉ አለመግባባት የብዙ አባላትንና ደጋፊዎች የትግል መንፈስ ማቀዝቀዙ፣ በዉጭ በሚገኙ ድጋፍ ሰጭ ድርጅቶም ዉስጥ ልዩነት እንዲፈጠር ምክንያት መሆኑ የሚካድ ሲሆን በአመራሩ ዉስጥ የታየዉ ችግር ዉሽንፍር በቅንጅት ዩኬ አመራር ዉስጥ የተለያዩ የወገናዊነት ዝንባሌዎችና ቡድናዊ ስሜቶች ወይም መሳሳቦችን ማጫሩ አልቀረም:: ሆኖም ግን ግለሰባዊ ስሜቶች ቢንጸባረቁም እንደ ድርጅት ግን «ቅንጅት አንድ ነዉ» የሚለዉ መስመር ሲራመድ ቆይቷል:: የአንጃኝነት አቀንቃኝነት መንፈስ ጊዜዉን ጠብቆ መከሰቱ ባይቀርም ብዙዎቹ አባላት የድጋፍ ሰጭነትን ሚናና የፓርቲን አመራር ልዩነት በመገንዘባቸዉና ጉዳዩ በጥንቃቄ በመያዙ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ልዩነቱ ገጦ ሳይወጣ ተሸፍኖ ሊቆይ ችሏል:: ድጋፍ ድርጅቱ በቅንጅት ከፍተኛ አመራር ዉስጥ የተፈጠረዉ አለመግባባት በድርድር ወይም በሽምግልና እንዲፈታ፣ መቻቻል እንዲኖርና የድርጅቱ አንድነትና ሕልዉና አደጋ ላይ እንዳይወድቅ በየጊዜዉ ባወጣቸዉ መግለጫዎች ተማጽኖ ከማቅረብ፣ ማሳሰቢያና ምክር ከመሰጠት ዉጭ አንዱን ወገን ደግፎ ሌላዉን በመኮነን ቅራኔዉን በማጦዝ የችግሩ አካል እንዳይሆን በመጠንቀቅ የአንድነትን መንፈስ ሲያራምድ መቆየቱ የብሰለቱ ምልክት ነበር::

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ሃላፊነት በጎደለዉ አኳኋን በድርጅት ዉስጥ የራሳቸ ቡድን ፈጥረዉ ልዩነትን ባራመዱ የአመራር አባላት ምክንያት ሲደረግ የነበረዉ የአንድነት መጠበቅ ጥረት ሁሉ ብላሽ ሆኖ በአሁኑ ወቅት ቅንጅት ዩኬ በከፍተኛ ቀዉስ ዉስጥ ወድቋል:: የችግሩ መነሻ በቅንጅት አመራር ዉሰጥ በተፈጠረዉ ልዩነት ሳቢያ ዉስጥ ዉስጡን ሲንተከተክ የቆየዉ የቡድን አቀንቃኝነት ስሜት እያደገ መጥቶ ጊዜዉን ጠብቆ ገንፍሎ መዉጣቱና ድጋፍ ድርጅቱ ከቋቋመበት ዓላማና ከመተዳደሪያ ደንቡ ዉጭ ከአንድ ወገን ጋር ለመለጠፍ የተደረገዉ ድርጊት ያስከተለዉ ክሰተት ነዉ:: ሕግና መርህን በመጣስና በማክበር መካከል የተፈጠረ የአቋም መጣረስ ዉጤት ነዉ::

በቅንጅት አመራር ዉስጥ ችግር ቢፈጠርም ቅንጅት ዩኬ እንደ ድጋፍ ድርጅት በኦፊሴል ሲያራምድዉ የቆየዉ መሠረታዊ መርህ «ቅንጅት አንድ ነዉ» የሚል ነዉ:: ስለሆነም ችግሩ ይህን መሰረታዊ መርህ በመጣስ ከብዙሃኑ የድርጅቱ አባላትና ደጋፊዎች ዕዉቀትና ይሁንታ ዉጭ ድርጅቱን በብልጣብልጥነት ጠልፎ «ዴሞክራቲክ ቅንጅት» ከሚሉት ወገን ጋር ለመለጠፍ በአድማ የሚንቀሳቀሱ የአመራር ኮሚቴዉ አባላት የሚያራምዱት አቋምና አካሄድ ነዉ:: ግለሰቦች ወይም ቡድኖች የሚፈልጉትን የፓለቲካ መስመር የማራመድ መብታቸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ጠቅላላ ጉባኤ ተጠርቶ እንደ ድርጅት ግን አባላት በጉዳዩ ላይ ዉይይት አድርገዉ በጋራ ከዉሳኔ ላይ ሳይደርሱ አንድን ድርጅት በቆረጣ አካሄድ የአንድ ወገን ተቀጽላ ማድረግ ህገወጥ ከመሆኑም በላይ ዴሞክራሲያዊም አይደለም በማለት የድርጀቱ ሊቀመንበርና ጸሐፊ በመርህ ላይ የተመሰረተ አቋም በመያዝ እርምጃዉን ተቃዉመዋል:: በጥቅሉ የችግሩ መነሻ በአመራር ኮሚቴዉ ዉስጥ ያሉ በረጅም ገመድ የሚጎተቱ ተስፈኞች «የሚያንጸባርቅ ሁሉ ወርቅ» የሚመስላቸዉን የዋሆችን አጃቢ ወይም «ኮንቶርኖ» በማድረግ «ቅንጅት አንድ ነዉ» የሚለዉን አቋም የሚያራምዱ ግለሰቦችን በማሰወገድ ተልዕኳቸዉን ለማሳከት ያደረጉት በአድማ ላይ የተመሰረተ እንቅስቃሴ ነዉ::

የአድማዉ መሪዎችና ተከታዮቻቸዉ የአመራር ኮሚቴዉ የአንድ ዓመት የሥራ ዘመን ማብቃቱን እያወቁ፣ የድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ በሚያዘዉ መሠረት ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲጠራና አመራሩ የተሰጠዉን ማንዴት ለሕዝብ እንያስረክብ በተደጋጋሚ የቀረበዉን ሐሳብ «በዴሞክራሲያዊ የድምጽ ብልጫ» ዉድቅ በማድረግ ሲያጓትቱ ከቆዩ በኋላ ዉስጣዊ ዝግጅታቸዉ መጠናቀቁን እርግጠኛ ሲሆኑና አመቺ ጊዜ ሲያገኙ ጠቅላላ ጉባኤ ተጠርቶ «ብዙሃኑን ያቀፈዉ የዲሞክራቱ ቅንጅት» አመራር አባላት በእንግድነት ተገኝተዉ ቡራኬ



---

1Crowndale Road London NW1 1TU Tel/Fax: 020 7168 9893 E-mail: kinijit97@yahoo.co.uk

ወይም አመራር እንዲሰጡ መደረግ አለበት የሚል አቋም አራምደዋል፡፡ በተቃራኒውም ሊቀመንበሩና ጸሐፊዉ ድጋፍ ድርጅቱን በገንዘብ፣ በሞራልና በማቴሪያል የረዱ፣ በጸሐይና በዉርጭ እየተጠበሱ ድምጻቸዉን ሲያሰሙ የነበሩ አባላትና ደጋፊዎች ሳይወያዩበትና ሳይወስኑ በወገንተኛነት አካሄድ አንደኛዉን ወገን ማቅረብና ሌላዉን ማግለል የድርጅቱን አንድነት የሚያናጋ፣ ከመርህም ሆነ ከሕግ አንጻር ችግር የሚያስከትል መሆኑን፣ ቅንጅት ዩኬ የትኛዉን ወገን ይደግፍ የሚለዉ ለጠቅላላ ጉባኤዉ ቀርቦ መወሰን እንዳለበት፣ ይህም ካልተቻለ ግብዣዉ ለሁለቱም የቅንጅት ቡድኖች እንዲሆን፣ ይህ ካልሆነ ግን ከየትኛዉም ወገን ሰዉ ሳይጋበዝ ጠቅላላ ጉበኤዉ እንዲጠራ በተደጋጋሚ በመለማመጥና በልመና ጭምር ለማስረዳት ቢሞክሩም ጥረቱ ሊሳካ አልቻለም፡፡ በተለይም «ዴሞክራሲያዊ ነዉ» ተብሎ የሚነገርለት ወገን አዲስ ድርጅት በመመሥረት ሂደት ላይ መሆኑን በይፋ እየገለጸ ባለበት ወቅት ቅንጅትን ለመደገፍ በተቋቋመ ድጋፍ ሰጭ ድርጅት ስብሰባ ላይ ተገኝቶ አመራር እንዲሰጥ መጋበዝ በማንኛዉም መለኪያ ትክክል ሊሆን እንደማይችል ለማስረዳት የተደረገዉ ሙከራ «አዉቆ የተኛ ቢጠሩት አይሰማም» እንደተባለዉ ሆኗል፡፡

ዴሞክራሲን፣ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን አራምዳለሁ የሚል ቡድን የዴሞክራሲ መቋጫ የሆነዉን የሕዝብን መብትና ምርጫ በመቀበል ከድርጅቱ ጎን ተሰልፈዉ የታገሉና አስተዋጽኦ ያደረጉ አባላትና ደጋፊዎች አብይ በሆኑ ወቅታዊ የድርጅቱ ጉዳዮችና መከተልም ስለሚገባዉ የትግል አቅጣጫ ምንም ተጽዕኖ ሳይደረግባቸዉ በነጻነት በግልጽነት ዉይይት አድርገዉ ከዉሳኔ ላይ እንዲደርሱ መድረክ መፍጠር ሲገባዉ በራሱ ቡድናዊ ዉሳኔ ከአንዱ ወገን ጋር ለመደረብ መሞከሩ የሚገርም ባይሆንም ተቀባይነት ሊኖረዉ አይችልም፡፡ አግባብነት በሌለዉ አካሄድ ከሕዝብ ጀርባ ድርጅቱን ለመጥለፍ የተደረገዉን ሃላፊነት የጎደለዉ ስታሊናዊ አሰራር ዴሞክራሲያዊ ነዉ ያሉበትን ምስጢር የሚያዉቁት የቡድን አራጋቢዎች ብቻ ናቸዉ፡፡

የቡድኑ አባላት ከምክንያታዊነት ይልቅ ጭፍንነትን፣ ከአንድነት ይልቅ አንጃኝነትን፣ ከድርጅታዊ መሰረታዊ ዓላማ ይልቅ ቡድናዊ ፍላጎትን ለማራመድ በወንዝ ልጅነት፣ በጓደኝነት፣ በቤተሰብ ትስስርና በወዳጅነት በመሳሳብ በተደጋጋሚ የቀረበዉን ልመናና ማሳሰቢያ በመናቅ፣ በዕብሪትና በግብታዊነት የወሰዱት አፍራሽ እርምጃ አዲስ ነገር ባይሆንም አስተዛዛቢ ነዉ፡፡ በማስመሰል ድራማ የዴሞክራሲን ቅኝት በመዝፈን፣ ግን ራስን ከሕዝብና ከሕግ በላይ በማድረግ፣ የቀረቡ ምክንያታዊ አማራጭ የመፍትሄ ሀሳቦችንና አስተያየቶችን ሁሉ አንድ ጊዜ « መአህድ/ መኢአድ ይሸታል»፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ «የደርግ-ኢሰፓ አሰራር» በማለት «የብዙሃን ዉሳኔ» በሚል ሽፋን ዉድቅ በማድረግ ዓላማቸዉን አራምደዋል፡፡ ቡድኑ ጠቅላላ ጉባኤ ተጠርቶ ህዝብ ከመወሰኑ በፊት ድብቅ ዓላማዉን በማራመድ የድርጅቱን ጽ/ ቤት፣ ፋይናንስ ንብረት በቁጥጥር ሥር ለማዋልና «ዴሞክራቲክ» ነዉ ከሚለዉ ወገን ጋር ለመጋባት በከፍተኛ ጥንቃቄ ሲንቀሳቀስ ቀይቶ ማርች 9 ቀን 2008 የተለያዩ ሕገወጥ የጉልበት እርምጃዎችን በመወሰድ የአንጃ አቀንቃኝነቱን በይፋ አረጋግጦአል፡፡ ቡድኑ በዕለቱና በተከታታይ ቀናት የወሰዳቸዉን ቅጽበታዊ አፍራሽ እርምጃዎችና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ሕዝብ እንዲያዉቃቸዉ ከዚህ በታች ዋና ዋናዎቹ ቀርበዋል፡፡

**1. አመራሩን ሙሉ በመሉ በቁጥጥር ሥር ማዋል፣**

ይህ ወቅትንና የሃይል ሚዛንን በማየት አቋም መለዋወጥን የፓለቲካ ዕዉቀት አድርጎ የሚንቀሳቀስ ቡድን ዓላማዉን ለማሳካት ቀላል ዘዴ ሆኖ ያገኘዉ ከሁሉ በፊት «አላራምድ አሉኝ ወይም መኢአድ ይሸታሉ» የሚላቸዉን ግለሰቦች በማስወገድ አመራሩን ሙሉ በሙሉ በቁጥጥር ሥር ማድረግ መሆኑን የከወሰዳቸዉ እርምጃዎች በተጨባጭ ያረጋግጣሉ፡፡ «እንቅፋቶችን» ለማስወገድ እንዲችል የሥራ አሰፈጻሚ ኮሚቴዉ አስቸኳይ ስብስባ እንዲጠራ ግፊት አድርጎ ማርች 9 ቀን 2008 በተካሄደዉ ስብሰባ ላይ «ሊቀመንበሩና ጸሐፊዉ ሥራ አጓተዋል፣ አላሰራም ብለዋል» የሚሉ ዉንጀላዎችን በመደርደርና ከሃላፊነት መነሳት



1Crowndale Road London NW1 1TU Tel/Fax: 020 7168 9893 E-mail: kinijit97@yahoo.co.uk

አለባቸዉ  የሚል መከራከሪያ በማቅረብ «የመተማመኛ ድምጽ» (ቮት ኦፍ ኮንፊደንስ) የሚለዉን አሰራር በመከወን አስቀድሞ በተደረገ ሴራ መፈንቅለ ሥልጣን አካሂዶ አመራሩን ለመቆጣጠር ችሏል:: ሹም ሽረቱ የተካሄደዉ ከመተዳደሪያ ደንቡ ዉጭና ኮሚቴዉ የሥራ ዘመኑን ከጨረሰ በኋላ በመሆኑ ድርጊቱ ሕገ-ወጥ ብቻ ሳይሆን ሥርዓት አልበኝነትም መሆኑን ለማስረዳት ሙከራ ቢደረግም የሴራዉ ግንባር ቀደም አቀንቃኝ የሆኑት አቶ ዘላለም « እኛ የምንደግፈዉ የዴሞክራሲዉን አንጃ ነዉ፣ እናንተም የምትፈልጉትን ሂዱና ደግፉ፣ መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ» በማለት ማሳረጊያ በመስጠታቸዉ ዉሳኔዉ ጸንቶ ሊቀመንበሩና ጸሐፊዉ ይዘዉት ከነበሩበት ቦታ ተነሰተዉ፣ በቦታዉም አቶ አበበ ቶሎሳ ሊቀመንበር፣ አቶ ብዘነህ ጽጌ ደግሞ ጸሐፊ ሆነዉ ተሻሹመዉ በደርጅቱ ዉሰጥ «ዴሞክራሲንና ቀልጣፋ አሰራር አሰፈነዋል»:: ከበሮዉን መሸከምና በአግባቡ መምታት አንድ መሆናቸዉን ወደፊት የምናየዉ ሲሆን፣ በጉልበት ሥልጣን መያዝ በምን መለኪያ ዴሞክራሲያዊ እንደሆነ የሚያወቀዉ ቡድኑ ብቻ ነዉ::

## 2. ጽ/ቤቱን በቁጥጥር ሥር ማዋል

ወገንተኛዉ ቡድን በቀጣይ የወሰደዉ እርምጃ በድርጅቱ ጽ/ቤት ዉስጥ የሚገኘዉን ማንኛ ዉንም ንብረት፣ ሰነድና ገንዘብ በእጁ ማስገባት ነበር:: ሊቀመንበሩንና ጸሐፊዉን ከሃላፊነት አሰወግዶ አዲስ አመራር በመሰየም መንገዱን ከጠረገ በኋላ በዚሁ በማርች 9 ቀን ሌሎች አሳዛኝና አስቂኝ «ዴሞክራሲያዊ» እርምጃዎችን ወስዷል:: አንደኛ ጸሐፊዉ ሃላፊነት ወስዶ ይሠራባቸዉ የነበሩ የድርጅቱን  ሰነዶች በተለይም ፋይናንስ ነክ የሆኑ ሰነዶችን ርክክብ እንዲደረግ እንኳን ሳይጠይቅ ከቢሮ አዉጥቶ ወስዷል:: ሁለተኛ ጸሐፊዉ የቢሮ ሃላፊ ሆኖ ከሁለት ዓመት በላይ ሲገለገልበት የነበዉን ኮምፒዩተር እና የድርጅቱን የኤሜል መክፈቻ (ፓስ ወርድ) በመቀየር ጸሐፊዉ መጠቀም  እንዳይችል (አክሴስ) እንዳያደርግ አድርጓል:: (ፓስ ወርዱ ሊቀየር የቻለዉ በረዳትነት የይሰሩ የነበሩት አቶ ብዙነህ ጽጌ እምነት አጉደለዉ ኮዱን አሳልፈዉ በመስጠታቸዉ ነዉ:: ጉዳዩ ከታወቀ በኋላ ኮምፒተሩ (ሃርድ ዌር) ከዘረፋ ድኖ በጸሐፊዉ እጅ ይገኛል)::  ሶስተኛ ሌላ ሰዉ በተለይም ጸሐፊዉ ከቢሮ መግባት እንዳይችል ለጽ/ቤቱ አከራይ ግለሰብ  የቃልና የጽሑፍ ማሰጠንቀቂያ በመሰጠትና ተጽዕኖ በማሳደር የቢሮዉ በር ቁልፍ እንዲቀየር አድርጓል:: በዚህም ጸሐፊዉ ቢሮ የመግባት መብቱን ተነፍጎአል:: **(አባሪ አንድን ይመልከቱ)**:: ቡድኑ ለቢሮ አከራዩ በሰጠዉ ማሰጠንቀቂያ ደብዳቤ ላይ የሊቀመንበሩንና የፀሐፊዉን እንደዚሁም የአንድ ሌላ ሰዉ ሰም በመጨመር ዉሳዉ የጠቅላላ ኮሚቴዉ ለማስመሰል ያደረገዉን ብልጠት ልብ ይሏል::

## 3. የድርጅቱን ፋይናንስ መቆጣጠር

በድርጅቱ ህገ ደንብ መሠረት የባንክ ሂሳብ የሚንቀሳቀሰዉ በሊቀመንበሩ፣ በጸሐፊዉና በገንዘብ ያዡ ፊርማ ነዉ:: ገንዘብ ለማዉጣት ቢያንስ ከሶስቱ ሁለት ሰዎች መፈረም አለባቸዉ:: ችግር ፈጣሪዉ ሞገደኛ  ቡድን ሊቀመንበሪና ጸሐፊዉ ከሃላፊነት ቦታቸዉ እንዲወገዱ ያደረገበት ዋናዉ ምክያት የድርጅቱን ገንዘብ በእጁ ማስገባትና ለፈለገዉ ዓላማ መጠቀም እንዲችል ስለፈለገ ነዉ:: በመሆኑም ባደረገዉ ከፍተኛ ጥንቃቄ የተሞላበት ምስጢራዊ እንቅስቃሴ ገንዘቡ «ለመኢአድ ከመሰጠቱ በፊት» ፈራሚዎችን በመቀየር የድርጅቱን ገንዘብ በቁጥጥሩ ሥር ለማዋል ችሏል:: ቡድኑ መንፈቅለ ሥልጣን  ባካሄደ በሶሰተኛዉ ቀን ለኢች ኤስ ቢሲ ዘጠኝ አባላት ያሉት አዲስ የሥራ አመራር ኮሚቴ የስም ዝርዝርና ፊርማ የያዘ ዉሳኔና የአዲሶቹን ፈራሚዎች ስም የያዘ ማመልከቻ በማቅረብ አቶ አበበ ቶሎሳ (ሊቀመንበር) አቶ ብዙነህ ጽጌ (ጸሐፊ) የሂሳብ አንቀሳቃሽ ፈራሚዎች ሆነዉ መሰየማቸዉንና የኮረስፓንደስ አድራሻዉም መለወጡን ከባንኩ የተገኘዉ መረጃ ያረጋግጣል:: ባንኩ አዲሶቹን ፈራሚዎች የተቀበለዉ ጠቅላላ ጉባኤ የሰየማቸዉ  አዲስ አመራር አባላት ናቸዉ በሚል የዘጠኝ ሰዎች ስም ዝርዝር የያዘና በድርጅቱ «ሌተር ሄድ» የተጻፈ ደብዳቤና ቃለ ጉባኤ ስለቀረበለትም መሆኑን ገልጾአል:: **(አባሪ ሁለትን ይመልከቱ)**::



1Crowndale Road London NW1 1TU Tel/Fax: 020 7168 9893 E-mail: kinijit97@yahoo.co.uk

ለመሆኑ ድርጅቱ ስንት ገንዘብ አለዉ? የሚል ጥያቄ በአንባቢዎች አዕምሮ መመላለሱ አይቀርም። የገቢና ወጭ ሰነዶች በሙሉ በመወሰዳቸዉ ዝርዝር መረጃ ለመስጠት ባይቻልም ችግሩ ከመፈጠሩ በፊት በቢሮዉ በኩል ከተላከዉ የባንክ ስቴትሜንት መረዳት እንደሚቻለዉ እስከ ፌብሯሪ 28 ቀን 2008 ድረስ በከረንት አካዉንት ዉሰጥ 11723.88 (አባሪ ሶስትን ይመልከቱ)፣ በቁጠባ ሂሳብ (ሴቪንግስ አካዉንት) 5000.00 በጠቅላላዉ 16723.88 (አስራ ስድስት ሺ ሰባት መቶ ሃያ ሶሰት ፓዉንድ በባንክ ዉስጥ ይገኛል። በአሁኑ ወቅት ስላለዉ ሁኔታ በኛ በኩል የሚታወቅ ነገር የለም። በመሆኑም ከፌብሯሪ 28 ቀን በኋላ ለሚሆነዉ ሁሉ ተጠያቂዎቹ በአሻጥር ራሳቸዉነ በሃላፊነት ያስቀምጠትና እጃቸዉን በሕዝብ ገንዘብ ላይ ያሳረፌት መሆናቸዉን አባላትና ደጋፊዎች፣ ጠቅላላዉ ማህበረሰብና የሚመለከታቸዉ ወገኖች ሁሉ ይረዱታል ብለን እናምናለን።

## 4. የስም ማጥፋት ዘመቻ መካሄድ

ሊቀመንበሩና ጸሐፊዉ ከአባላት ዉሳኔና ዕዉቀት ዉጭ ድርጅቱን ጠልፎ ወደሌላ አቅጣጫ መዉሰድ ወይም ከአንድ ወገን ጋር ለመለጠፍ መሞከር ትክክል አይደለም ብለዉ መቃወማቸዉ ትልቅ ወንጀል ሆኖ ወገንተኛዉ ቡድን ከፍተኛ የስም ማጥፋት ዘመቻ ያካሂዳል። ያለቦታዉ የሚነፋ ወናፍ እንኳን ብረት በረዶም እንደማያቀልጥ ቢታወቅም «ዉሸት ሲደጋገም ዕዉነት ይሆናል» ነዉና አንዳንድ ጉዳዮችን በሐቅ መግለጽ አግባብነት አለዉ። ከሞቀበት መዝፈን የሚወዱትና የወቅቱን የሃይል ሚዛን አይተዉ ከቤት ሥራ መልስ ወደ እንቅስቃሴዉን የተቀላቀሉ ብልጣብልጥ የድል አጥቢያ አርበኞች በስም ማጥፋት ላይ ተሰማርተዉ « ሥራ ተበደለ፣ ትግል ተጓተተ፣ ጸሐፊዉ ኮምፒዩተር ሰረቀ ወዘተ» የሚሉትን ፌዝና በህብረተሰቡ ዉስጥ ተሰሚነት ያላቸዉን ግለሰቦች በመቅረብና ስልክ በመደወል « ዕገሌ ዕንደዚህ አለህ» በማለት የሚካሄደዉ ተራ የመንደር ወሬ ይቅርና የድርጅቱን ገንዘብ መባከን አስመልቶ ስለሚነዛዉ አሉባልታ ሕዝብ ዕዉነቱን ማወቅ አለበት።

የገንዘብ ብክነትን አስመልክቶ ሁለት ዓይነት የስም ማጥፋት ዘመቻዎች ይካሄዳሉ። አንደኛዉ ሊቀመንበሩና ጸሐፊዉ ለባንኩ ደብዳቤ በመጻፍ ገንዘብ ያዡን በማግለል የድርጅቱን የባንክ ሂሳብ በሁለቱ ፊርማ ብቻ እንዲንቀሳቀስ ለማድረግ ሞክረዋል የሚል ክስ ነዉ። ይህ ግን ከዕዉነት የራቀ ነዉ። የተጻፈዉ ደብዳቤ ይዘት ስም አጥፊዎቹ እንደሚያወሩት ገንዘብ ያዡን በማግለል ሊቀመንበሩና ጸሐፊዉ ብቻ ፊራሚ ናቸዉ የሚል ሳይሆን የባንክ ፊራሚዎች ለዉጥ በሚደረግበት ወቅት አሁን ካሉት ፊራሚዎች ዉስጥ <u>ቢያንስ</u> ከሶሰቱ በሁለቱ ፊርማ መረጋገረጥ አለበት የሚልና የድርጅቱ ገንዘብ ከማንኛዉም አጭበርባሪ እጅ እንዳይገባ ባንኩ ጥንቃቄ እንዲያደረግ ሃላፊነትን ከመወጣት አኳያ የተጻፈ ደብዳቤ ነዉ። ሐቁ ይህ ሲሆን አንባቢዎች የራሳቸዉን ግንዛቤ እንዲወስዱ በማስረጃነት የቀረበዉን የደብዳቤዉ ቅጅ እንዲያዩ እንጋብዛለን። (አባሪ **አራትን ይመልከቱ**)።

ሁለተኛዉ ገንዘብ ነክ አሉባልታ ጸሐፊዉ ከድርጀቱ ብዙ ገንዘብ ወስዷል የሚል ነዉ። ጸሐፊዉ ለሁለት ዓመታት ያህል ቢሮዉን በሃላፊነት መያዙ ዕዉነት ሲሆን ክፍያን አስመልክቶ የሚወራዉ ግን ከዕዉነቱ በጣም የራቀ ነዉ። ድርጅቱ በአዲስ መልክ ተዋቅሮ ጸሐፊዉ ሃላፊነቱን ከተከረከበበት ከጃንዋሪ 2006 እስከ ጥር 2007 ድረስ ከድርጅቱ ምንም ዓይነት ገንዘብ አልተከፈለዉም። ይህንን ሐቅ በወቅቱ በአመራር ላይ የነበሩና አሁንም ያሉ ሁሉ ሊያረጋግጡት የሚችሉት ጉዳይ ነዉ። የተሰጠዉ ሙሉ በሙሉ ነጻ አገልግሎት ነዉ። ሆኖም ግን በሁለተኛዉ ዓመት ማለትም ከፌብራሩ 2007 - አክቶበር 2007 ድረስ ዛሬ ስም በማጥፋት ላይ የተሰማሩትን ግለሰቦች ጨምሮ ከሚቴዉ በሰጠዉ ዉሳኔ ከ540 (አምስት መቶ አርባ ፓዉንድ) ለመጓጓዣ ወጭ የተከፈለዉ መሆኑን ያምናል። ይህም በሰነድ ላይ የተቀመጠ

ነዉ:: ከዚህ ዉጭ ፀሐፊዉ ሥልጣኑን ተጠቅሞ ያለአግባብ ዘግኖ ለግል ጥቅሙ ከኪሱ የከተተዉ ድርጅት ገንዘብ አለመኖሩን ያረጋግጣል:: በተረፈ ግን የድርጅቱ የፋይናንስ ሰነድ ተመርምሮ በሥልጣን ብልግና ያለ አላግባብ የወሰደዉ ገንዘብ መኖሩ ከተረጋገጠ ሃላፊቱን ለመዉሰድ ዝግጁ መሆኑን ሰሕዝብ ግልጽ ማድረግ ይፈልጋል:: ከዚህ ሌላ ከቅርብ ጊዜ በፊት የተሰበሰበ 233 (ሁለት መቶ ሰላሳ ሶስት ፓዉንድ) የአባልነት መዋጮ ከጸሐፊዉ ዘንድ ይገኛል:: ገንዘቡ አዲስ ለሚመረጠዉ ኮሚቴ ወይም አባላት ለሚወክሉት ሰዉ ወይም አካል ይሰጣል::

**የድርጅቱ ንብረት በሚመለከት**

የድጋፍ ድርጅቱ ንብረት ከጽህፈት ሥራ ጋር የተያያዙና ያልተያያዙ ልዩ ልዩ ተንቀሳቃሽ ቁሳቁሶችንና ሰነዶችን ያጠቃልላል:: ቀደም ሲል ንብረቱ በሙሉ በቢሮ ዉስጥ የነበረ ሲሆን ችግር ፈጣሪዊ ቡድን ልዩ ልዩ ሰነዶችን ከሕግ ዉጭ ከቢሮ አዉጥቶ ወስዷል:: በአሁኑ ወቅት ምን ዕቃ ወጥቶ ምን እንደ ቀረ ማረጋገጥ አይቻልም:: ከዚህም በተጨማሪ የቅንጅት የልኡካን ቡድን ለንደን መጥቶ በነበረበት ወቅትና ከዚያም በፊት በድርጅቱ ስም ተነስተዉ የነበሩና ለጽ/ቤቱ መግባት የነበረባቸዉ ልዩ ልዩ ኦዲዮ ቭዣሎችና ፎቶግራፎች ተደጋጋሚ ጥያቄ ቢቀርብም ፈቃደኛ ባለመሆናቸዉ በአቶ ደረጀ ደስታ እጅ የሚገኙ መሆናቸዉ ሊታወቅ ይገባል:: ከዚህ ሌላ ተሰረቀ የተባለዉ አንድ ኮምፒዩተር በጸሐፊዉ እጅ ይገኛል:: የቢሮዉ ቁልፍ ተቀይሮ ጸሐፊዉ ቢሮ መግባት ከተደረገ በኋላ ከቢሮዉ ዉሰጥ ለሚጠፋዉ ማንኛዉም ንብረት ጸሐፊዉ ሃላፊነት አይወሰድም::

**7. የቅንጅት ዩኬ የወደፊት ዕድልና አቅጣጫ**

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረዉ በቅንጅት ዩኬ ዉስጥ ለተፈጠረዉ ችግር ዋናዉ መንሰኤ ሕዝብ የሰጣቸዉን የዉክልና አደራና ድርጅቱ የተቋቋመበትን ዓላማ ክደዉ በሽፍጥ ወደ ሌላ አቅጣጫ በመወሰድ በገጸ-በረከትነት ለማቅረብ በአመራሩ ዉስጥ የነበሩ በቡድን ስሜት የሚንቀሳቀሱ ወገኖች ያደረጉት አካሄድና ይህ ትክክል አይደለም፣ ትክክለኛዉ መንገድ በጉዳዩ ላይ አባላት ተወያይተዉ በጋራ የሚወሰኑትን ተግባራዊ ማድረግ ነዉ የሚል የአቋም ልዩነት ነዉ:::: ተወደደም ተጠላ የቅንጅት ዩኬ የወደፊት አቋም፣ የትግል አቅጣጫና የሥራ ግንኙነት በጥቂት የአመራር አባላት ሳይሆን፣ ገንዘባቸዉንና ጊዜያቸዉን መስዋዕት ባደረጉ አባላትና ደጋፊዎች መወሰን ይገባዋል:: የድርጅቱ ዕድል የሚወስነዉ በጠቅላላ ጉባኤዉ እንጂ የሥልጣን ዘመኑን የጨረሰ አመራር ኮሚቴ ሊሆን አይችልም:: ጠቅላላ ጉባኤ ሳይጠራና ብዙሃኑ አባላት በጉዳዩ ላይ በግልጽና በነጻነት ተወያይተዉ ዉሳኔ ሳይሰጡ ድጋፍ ድርጅቱን በቆረጣ ስልት ከአንድ ወገን ጋር መለጠፍ ሕዝባዊም ዴሞክራሲያዊም ሊሆን አይችልም:: ስለሆንም አስፈላጊዉ ቅድመ ዝግጅት ተደርጎ ጠቅላላ ጉባኤዉ እንደሚጠራ በድርጅቱ ዉስጥ የተፈጠረዉ ችግርም ሆነ የድጋፍ ድርጅቱ የወደፊቱን አቅጣጫ በዉይይት መልክ እንደሚይዝ በማወቅ አባላት በወቅቱ ተሳታፊ በመሆን የበኩላቸዉን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ከወዲሁ ጥሪያችንን እናቀርባለን::

**8. ምስጋና**

እንደታሰበዉ ዉጤቱ ባይሰምርም፣ በድርጅቱ ወስጥ የተፈጠረዉ ችግር በሽምግልና እንዲፈታ ሁለቱን ወገኖች ለማቀራረብ ከፍተኛ ጥረት ላደረጉና ጉዳዩን በሽምግል ለማየት ፈቃደኛ በመሆን ያለ ምንም የተለየ ተልዕኮ ችግሩን በሐቅ ለመፍታፍ ጊዜያቸዉን ላጠፉ አስታራቂ ሽማግሌዎች ልባዊ ምስጋና እናቀርባለን::

ቅንጅት አንድ ነዉ!!!.



1Crowndale Road London NW1 1TU Tel/Fax: 020 7168 9893 E-mail: kinijit97@yahoo.co.uk

ኃይለማርያም ለገሰ
ዋና ጸሐፊ

**Contact: hethio2004@hotmail.com**



1Crowndale Road London NW1 1TU Tel/Fax: 020 7168 9893 E-mail: kinijit97@yahoo.co.uk